የሰራው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ

/ለወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣
ወታደር፣ ምሁር፣/

መብትና ጥቅም

የሚታገል ጋዜጣ

ቁጥር 61 ቀን 16/12/69

ስለሁለቱ ትግል::

1. <u>መግቢያ</u>

ይህንን "የሰራው ህዝብ ድምፅ" ጋዜጣ ቁጥር አገኝተው የሚያነቡ፣ ወይንም ደግሞ ይዘቱን በወሬ ደረጃ የሰሙ አንዳንድ ሰዎች፣ መኢሶን ዛሬ ይዞት የወጣውን የትግል ጥሪ ከቀድሞው የተለየ አድርገው ሊመለከቱት እንደሚችሉ እንገምታለን:: ይሁን እንጂ፣ እስከዛሬም ድረስ ሆን ብለው ውዥንብር ሲነዙ ከቆዩት የለየላቸው አድሃሪያንና አናርኪስቶች በስተቀር፣ የፖለቲካ መስመር ትግልን ምንነት በትክክል ለመረዳት ካልቻሉት ሰዎች በስተቀር፣ የመኢሶንን የፖለቲካ መስመር በጥሞና የተከታተሉት ሁሉ፣ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ አንዳችም "ከቀድሞው የተለየ አዲስ የፖለቲካ መስመርን" እንደማያነቡ እምነታችን ነው:: የመኢሶንን ፕሮግራም የመጀመሪያ ገጾች እንኳን ያገላበጠ ሰው፣ የድርጅቱን የፖለቲካ ትግል መስመር የሚረዳው ይሆናል:: በመኢሶን ፕሮግራም መግቢያ ውስጥ እንደተገለፀው:—

"መኢሶን ለኢትዮጵያ ጭቁኖች የተሟላ ነፃነትና ለሶሻሊዝም ቆሟል:: ለዚህ አላማ ከሚታገሉ ሀይሎች ጋር ሁሉ፣ የትግል አንድነት ለመመስረት እጁን ይዘረጋል:: ለቆመለት አላማ ያለንዳች ማወላወል <u>በምስጢር፣ በይፋ፣ በህጋዊ መንገድና በህገወጥነት፣ በሰላማዊ መንገድና በአመጽ፣</u> እንደሁኔታውና እንደሁኔታው በሚለዋወጡ ታክቲኮች፣ ምንም ጊዜ ምንም ሁኔታ በማይለውጠው ቆራጥነትና ታታሪነት የሚታገሉ አባላቶቹን አስተባብሮ ለኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ነፃነትና እድገት ተሰልፍአል:: የኢትዮጵያ ጭቁኖች የሚያደርጉትን የተባባለ ትግል ከዳር እስከዳር አስተባብሮ፣ ለዲሞክራሲያዊ አብዮታዊ አመራር ለመስጠት <u>በጭቁን ህዝቦችና በታሪክ ፊት የተቀበለውን አደራ እስከመጨረሻው ይጠብቃል::</u> ጭቁኖች በትግላቸው እንደሚገፉ፣ በትግል እሳት የተፈተኑ አባላቱ አብዮታዊ ግዴታቸውን ከመፈፀም ወደኋላ እንደማይሉ የጠነከረ እምነት አለው:: ስለሆነም፣ የወሰደውን ጊዜ ይውሰድ እንጂ፣ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ወደ ነፃነትና ወደ ሶሻሊዝም ለሚያደርጉት ጉዞ የመጨረሻው ድል የነርሱ እንደሆነ ቅንጣት አንጠራጠርም::"

እነዚህ ቃላት የተፃፉት በመጋቢት ወር 1968 ዓ.ም. መኢሶን ምስጢራዊ መዋቅሩን ሳይገልፅ፣ ህልውናውን በፕሮግራሙ አማካይነት ባሳወቀበት ጊዜ ነበር:: መኢሶን በዚያን ወቅትና አሁንም፣ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ወደ ተግባር ሊያደርሰው የማይችል ሀይል መሆኑን ቢያውቅም፣ ከታህሳስ 1968 ዓ.ም. ጀምሮ፣ አንዳንድ አባሎቹን በህጋዊ መስክ አሰማርቶ ሲታገል እንደቆየ የሚታወቅ ነው::

መኢሶን ከመጀመሪያው <u>ይህንን</u> የትግል መስክ የመረጠው፣ በነበረው አመቺ ሁኔታ ያቅሙን አሟርቶ አብዮቱን ትክክለኛ ፈር ለማስያዝ፣ ሰፊው ህዝብ መብቱንና ጥቅሙን በትክክል እንዲረዳ ለማገዝና በመደራጀት ንቃቱንና ድርጅቱን ለማዳበር የሚያስችለው ሁኔታ ሁሉ እንዲፈጠር ለመርዳት ነበር:: በርግጥም ደግሞ፣ በዚህ ትግሉ አማካይነት፣ ሰፊው ህዝብ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን አላማዎች ተግባሮች በመጠኑም ቢሆን እንዲረጋገጡ፣ እርሱን ወክለው በድብቅ የተንቀሳቀሱትን ፋሺስቶችና ሌሎችንም አድሃሪያን አጋልጦ እንዲመነጥራቸው፣ በዚህም ትግሉ ንቃተ ህሊናውንና የድርጅት ደረጃውን ከፍ እንዲያደርግ ለማገዝ ተችሏል:: የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብና የኢትዮጵያ ተራማጆች በመተባበር ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ ተደጋግመው የተነሱትን የቀልበሳ ሙከራዎች ለማክሸፍ በመቻላቸው አብዮታችን ወደፊት ተራምዷል::

.../2

2. የትግል ስልት ለውጥ

ከጥቂት ወራት ወዲህ በኢትዮጵያ አብዮትና በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የተሰነዘረት አደጋዎች እስካሁን ከታዩት ሁሉ በላይ ከባድና አስጊ ሆነዋል::ባሁኑ ጊዜ፣ አገራችንና አብዮቱ በተለቀ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ውጥረት ውስጥ እንደወደቁና ሁኔታውም በየእለቱ እየተባባሰ እንደሚሄድ በአይናችን የምናየው እውነት ነው::

በፖለቲካ በኩል፣ ሰፊው ህዝብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹን ሊቀዳጅና በሙሉ ነፃነትና በህዝባዊ ሄይሉ በአብዮቱ ሊሳተፍ አልቻለም::እንዲያውም ባንዳንድ ክፍለ ሃገር —በሃረርጌ፣ በባሌ፣ በሲዳሞ፣ በከፋ፣ በጎንደር— ከፍተኛ እልቂት እየደረሰበት ነው::በተለይም በሃረርጌ ሰፊው አርሶአደር ህዝብ ባንደ ወገኑ ወራሪ አገሩን በወረሩት የሶማሊያ ወታደሮች እየተጨፈጨፈ ነው::በሌላ ወገን ደግሞ፣ የብሄር ትምክህተኝነት ነገስ የቀድሞዎቹ የመሬት ከበርቴዎች በፋሺስታዊ ጭካኔ በገፍ እየረሸኑት ነው::በነዚህ ክፍለ ሃገር የሚገኙት ህዝባዊ ድርጅቶች —የወዛደር፣ የገበሬ፣ የቀበሌ፣ የሴቶች፣ የወጣቶች ድርጅቶች— እየፈራረሱ ናቸው::.....

በኢኮኖሚ በኩል፣ የሸቀጣ ሸቀጥ መጥፋት፣ የእህል መወደድ፣ የዋጋ መናርና የስራአጥ መብዛት፣ ሰፊውን ህዝብ፣ በተለይም ሰፊውን የከተማ ህዝብ፣ በከባድ ችግር ውስጥ ጥለውታል:::..

በማህበራዊ ጉዳይ በኩል፣ በትምህርት፣ በጤናና በሌሎችም አገልግሎቶች በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ውስጥ የተጠቀሱት ተግባሮች ምንም ያህል ከስራ ላይ አልዋሉም::....

በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ፣ የአድሃሪዎቹ ከበባና ወረራ፣ እንደዚሁም የአብዮቱ ከውስጥ መቦርቦር በተፋጠነ እርምጃ በመካሄድ ላይ ይገኛሉ::በፊውዶ—ቡርዧው ቢሮክራሲ ውስጥ ቁልፍ ቦታዎችን የያዙ አድሃሪዎች የየራሳቸውን የቅጥረኛ ነፍሰገዳዮች ቡድኖች አቋቁመው፣ በደርጉም ውስጥ ሆነ ከዚያ ውጭ ያሉትን ተራማጆች ጨርሰው የመንግስትን ስልጣን ለመያዝ አሰፍስፈዋል::ስለዚህም የጊዜው ሁኔታ ከመቸውም ይበልጥ ለአብዮት ቅልበሳ እጅግ በጣም አመቺ ሆኖአል::

በንደዚህ አይነቱ የጠቀሰለ ውጥረት ወቅት፣ የኢትዮጵያ ተራማጆችና አገርወዳዶች ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው፣ ለሚወዷት እናት አገራቸውና ለአብዮታቸው በይፋ ለመዋደቅ መቻል ነበረባቸው:: ግን በዛሬው ወቅት ህጋዊው የትግል መስክ እየመነመነና እየጠበበ በመሄዱ ይህን የተቀደሰ ምኞት ከስራ ላይ ለማዋል ቀላል አልሆነም::ስለዚህም፣ መኢሶን አብዮቱን ትክክለኛውን ፈር ለማስያዝ፣ የአገራችንን ብሄራዊ ነፃነት ለማስከበርና የህዝቦችዋን አንድነት ለመጠበቅ በሚደረገው ጥረት፣ ምንም ታጽእና በማይናረው መንገድ፣ የበኩሉን ለማበርከት በማለት በህጋዊ ስራ ያሰማራቸውን አንዳንድ ጓዶች ወደህቡእ የትግል መስክ ለማዛወር ወስኖአል::መኢሶን ይህንን እርምጃ እንዲወስድ ካስገደዱት ምክንያቶች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው::

አንደኛ::በጥርና በየካቲት ወራት አብዮቱ ከተከላካይነት ወደአጥቂነት በተሸጋገረበት ወቅት፣ ሰፊው ህዝብ ነፃ አብዮታዊ እርምጃዎችን በመውሰዱ፣ ባንድ በኩል የውስጥ ፀረአብዮት ሄይሎች መፍጨርጨር ሲገቱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ እነዚህ ነፃ አብዮታዊ እርምጃዎች ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስትን አስደንግጠውት ነበር::ስለዚህም፣ ደርጉ የንኡስ ከበርቴውን መደብ ወላዋይነት በማሳየት፣ የቀበሌዎችን መታጠቅ አግዶ፣ እንዲያውም በማሰጠው ተስፋ አስቆራጭ ፕሮፓጋንዳ የቀበሌዎች ሞራል ሰበረ፣ በወሰዳቸው እንዳንዱ እርምጃዎች ደግሞ በቀበሌ መሪዎችና በወዛደሮች ላይ ጭቆናዎች ተፈፀሙ::ከመጋቢት ወር ጀምሮ በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች አብዮቱ እንደገና ወደተከላካይነት እንዲዘቀጥ ተደረገ::ከዚህም የተነሳ ይህች አገራችን በጭር ጊዜ ውስጥ ልትተካቸው የማትችል በርካታ ያሉ ቆራጥና ታታሪ አብዮታውያንና አገርወዳዶች በአድሃሪያን ጥይት ወድቀዋል፤ እየወደቁም ናቸው::

ሁለተኛ::አብዮቱ ከአጥቂነት ወደተከላካይነት ከተመለሰበት ምክንያቶች አንዱ፣ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እምነቱን በሰፊው ህዝብና በተራማጆች ላይ ሳይሆን፣ ይበልጡን በፊውዶ—ቡርዧው ቢሮክራሲ ላይ በመጣሉ ነው::በዚህም ሁኔታ በመጠቀም፣ አድሃሪዎች በተራማጆች መሀከል አለመተማመን እንዲሰፍን አድርገው ተራማጆችን ከፋፍለዋል፤ መኢሶንን በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ለማስመታት ሞክረዋል፤ የዛሬውም ስራቸው በዚሁ የማስመታትና የመምታት አላማ ዙሪያ እየተወጠነ ነው::እንዲያውም በፊውዶ—ቡርዧው ቢሮክራሲ ውስጥ ያሉ፣ ከሁሉ አድሃሪ የሆኑ ቡድኖች፣ የታወቁና በህጋዊ ስራ የተሰማሩ የመኢሶን ጓዶችን አንድ በአንድ እየገደሉ ለመጨረስ እንደወሰኑና ይህንንም ፋሺስታዊ አላማቸውን ከስራ ላይ ማዋል እንደጀመሩ መኢሶን ደርሶበታል:: በተጨማሪም፣ በሀረርጌ፣ በከፋ፣ በሸዋና በሌሎችም ቦታዎች ሃቀኛ ተራማጆች ይታሰራሉ፣ ይረሸናሉ:: አድሃሪዎች ሃቀኛ ተራማጆችንና ሰፊውን ህዝብ ለመነጣጠል የሚያደርጉትን መፍጨርጨር በከፍተኛ ደረጃ አፋፍመውታል::

ሶስተኛ::መኢሶን በአባልነት የሚገኝበትን "የኢትዮጵያ ማርክሲስት—ሌኒኒስት ድርጅቶች ህብረትን" የፈጠሩት አንዳንድ ድርጅቶችም በነዚህ የአድሃሪዎች ሴራዎች ላይ ነቅተው፣ ዋናና መሰረተኛ ቅራኔዎችን ለይተው፣ ለሃቀኛ ህብረት በመሰለፍ ፈንታ በአድሃሪዎች ወጥመድ ውስጥ በመውደቅ፣ በድርጅታችን ላይ የስም ማጥፋትና የማጥላላት ዘመቻ አካሂደዋል፤ እያካሄዱም ናቸው::

..../3

አንዳንዶቹም ራሳቸው ፈጥረው የሚነዙትን የስም ማጥፋያ ፕሮፓጋንዳ ራሳቸው ያምኑበት ይመስላል፡፡ ስለዚህም፡ ህብረቱ በዲሞክራሲያዊ አሰራርና በቅን ነገሮች ላይ የተመሰረተ መሆኑ ቀርቶ፣ አንድም እርምጃ ወደፊት ለመራመድ እንዳይችል ተሰንክሎ፣ ''የማይ ተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል'' እንደሚባለው ሁሉ፣ በወረቀት ላይ የሚቀሩ ፕሮግራሞችን ብቻ ደጋግሞ በመንደፍ ተወስኖአል፡፡

አራተኛ፡፡ የአብዮታዊት ኢትዮጵያን ህልውና ለማስጠበቅና አብዮቱ ስር እንዲሰድ ይጠቅማሉ በማለት፣ በህጋዊ ስራ በተሰማሩት ጓዶች አማካይነት መኢሶን ለጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና ለተራማጆች ህብረት በየወቅቱ ያቀረባቸውን አሳቦች በቅን መንፈስና ከአብዮቱ አንፃር በመመልከት ፈንታ፣ አሳቦቹ ከመኢሶን በመመንጨታቸው ብቻ ደርጉና አንዳንዶቹ ድርጅቶች በጥርጣሬ አይን እያዩአቸው ከስራ ላይ ሳይውሉ በመቅረታቸው ለውጥረት መፍትሄና ለአብዮቱ የተፈለገውንና የሚጠበቀውን ያህል አስተዋጽኦ ማድረግ አልተቻለም፡፡

ለምሳሌ ያህል፣ አሁን በየቦታው ደሙን በማፍሰስና አጥንቱን በመከስከስ ላይ የሚገኘውን ''ህዝባዊ ሰራዊት'' በሚመለከተው በኩል፣ አብዮታዊ አመራር እንዲኖረው፣ ብቁ የሆኑ የፖለቲካ አንቂዎች ከላይ እስከታች በብዙ ሺህ እንዲሰለፉበት፣ በተለይም ደግሞ ወደየመጡበት ተመልሰው ፀረአብዮትን በሚያውቀው አካባቢ እንዲቋቋም የቀረበው አሳብ ምንም ተቀባይነትን ሳያገኝ በመቅረቱ፣ ሰራዊቱ ዛሬ ብዙ ችግሮች ውስጥ ወድቆአል፡፡ በተጨማሪም መንግስት ሰፊውን ህዝብ በማመን በወቅቱ ስላላስታጠቀው አገሪቱ በምስራቅ በኩል እስከመደፈር ደርሳለች፡፡ ቢሮክራሲውን በሚመለከተው በኩል፣ በየሚኒስቴሩ፣ በየክፍለአገሩና በጦር ሃይሎች ውስጥ ያሉትን አድሃሪያን በወቅቱ በማስወገድ ፈንታ፣ ደርግ ስላቀፋቸው፣ ባሁኑ ወቅት አድሃሪው ቢሮክራሲ አንሰራርቶ ጠቅላላውን ሁኔታ ለቅልበሳ በማመቻቸት ላይ ይገኛል፡፡ ለኤርትራም ችግር፣ ፖለቲካዊ መፍትሄን በማስቀደም ፈንታ፣ ''ተገንጣዮቹን አንበርክከን በሁዋላ የፖለቲካ ውይይት እናካሄዳለን'' በሚል አስተሳሰብ በመመራቱ፣ ደርጉ አገሪቱንና አብዮቱን ወደማያዋጣ ጉዳና በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡.....

ሌሎችንም ምሳሌዎች ለመጥቀስ በተቻለ ነበር፡፡ ነገር ግን ደርግና በፍፁም አድርባይነት የታወሩት አንዳንዱ የህብረቱ ድርጅቶች መሪዎች፣ ከጥቂት ወራት ወዲህ ተጨባጩን ሁኔታና የሰፊውን ህዝብ ጥያቄዎች ለመከታተልና ለመረዳት በመሞከር ፈንታ፣ ድርጅታችንን ያጠቁና ያዳከሙ እየመሰላቸው፣ መኢሶን የሚያቀርባቸውን አሳቦችና መፈክሮች በመቃወም ላይ ብቻ ስለተኮሩ፣ ሃይላቸውን ሁሉ ሰብስበው አብዮቱን ለማራመድና ያገሪቱን ክብርና አንድነት ለመጠበቅ በማድረጉ ጥረት ላይ ለማዋል አልቻሉም፡፡

እላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ፣ መኢሶን የቀየሰውንና እስካሁንም ሲሰራበት የቆየውን ''የአብዮታዊ ሂስ'' መመሪያውን ያላንዳች ተጽእኖ ከስራ ላይ ሊያውል የማይችልበት ሁኔታ ተፈጥሮአል፡፡ ስለዚህም፣ መኢሶን አሁንም የሚያምንበትን ''የአብዮታዊ ሂስ'' መመሪያውን ያላንዳች ተጽእኖ ስራ ለመተርጎም ይቻለው ዘንድና፣ ስለኢትዮጵያ አብዮትና ስላገሪቱ አንድነት፣ ስለብሄራዊ ነፃነትና ስለወደፊቱ ትግል ያለውን አስተሳሰብ ለሰፊው ህዝብ ለማስተጋባት ይመቸው ዘንድ፣ እስከዛሬ በህጋዊ የትግል መስክ ያሰማራቸውን አንዳንዱ ጓዶቹን በህቡእ አሰማርቶ ለማታገል ወስኖአል፡፡

3. <u>አብዮቱንና አገሪቱን ለማዳን</u>

በዚህ በላይ እንደተመለከተው፣ አብዮታችንና የአገራችን አንድነት ባሁኑ ወቅት በከባድ ፈተና ላይ ይገኛሉ፡፡ የእለቱ ጥያቄ አብዮቱን ከቅልበሳ ለማዳንና ያገሪቱን አንድነት ለመጠበቅ ምን መደረግ አለበት የሚለው ነው፡፡ ዝርዝር መግለጫውን እስኪያወጣ ድረስ፣ መኢሶን ለጊዜው የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ባጭሩ ይጠቁማል፡-

<u>አንደኛ</u>፡፡ ባሁኑ ከባድ ወቅት ለመውጣት የሚቻለው፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ከዳር እስከዳር ሲንቀሳቀስ፣ እንደአንድ ሰው ሆኖ ሲነሳና የራሱን ታሪካዊ ድርጊቶች ለማከናወን ሲችል ብቻ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ፣ ሰፊው ህዝብ አብዮቱንና አገሪቱን በሚመለከቱት ጉዳዮች ላይ ሁሉ ሙሉ ተሳታፊ እንዲኖረውና ውሳኔዎቹን ሁሉ በሙሉ እምነት እንዲቀበል ያሻል፡፡ ለዚህ ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ ሰፊውን ህዝብ ለመንቀሳቀስና ለመነሳት የሚያስችሉት የዲሞክራሲ መብቶች መለቀቅ አለባቸው፡፡ ደርጉን ተቃውሞ፣ ወይንም በመንግስት ላይ ሂስ አቀረቡ በመባል ሃቀኛ የሰፊው ህዝብ ወገኖች መያዛቸው፣ መታሰራቸውና በዚህም የነፃ አስተሳሰብ መታፈን መቆም አለበት፡፡ ሰፊው ህዝብ በአዋጁ ያገኛቸውን ድሎች ሙሉ በሙሉ የመጠቀምና በስራ የመተርጎም እድል የሚያገኘው መብቶቹ ሲታወቁለት ነው፡፡

ሰፊው ህዝብ በነዚህ መብቶች በመጠቀም፣ አድሃሪ ቢሮክራቶችን ከላዩ ላይ አሽቀንጥሮ ጥሎ አዳዲስ ያስተዳደርና ያሰራር ዘዴዎችን ይፈጥራል፡፡ የሰፊው ህዝብ ንቃተህሊና ባጭር ጊዜ ውስጥ ይዳብራል፡፡ የመፍጠር ችሎታው ነፃ ስለሚወጣ፣ ሰፊው ህዝብ ችግሮቹን በራሱ ጥረትና ትግል ያሸንፋል፡፡ የመደቦች ሰልፍ ግልጽ ስለሚሆንና ትግሉም ፈር ይዞ ስለሚፋፋም፣ ሰፊው ህዝብ

የገዛ እራሱን በገዛ እጁ ለመጨበጥ የሚችልበት ወቅት ይቃረባል፡፡ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሰፊውን ህዝብ በመፍራት ወይም በመናቅ ሁሉንም የህዝቡን እንቅስቃሴ በፊውዶ-ቡርዧው የሲቪልና የሚሊተሪ ቢሮክራሲ አማካይነት ለመቆጣጠር መሞከሩን ከቀጠለ ግን፣ ይበልጡን ወደፀረአብዮት በፊር እየዘፈቀ ይሄዳል፡፡ የመጨረሻ መጨረሻም ከህዝቡ ጋር ይቃቃራል፣ ይቀራረ, ጣል፡፡

ሁለተኛ፡፡ ከነዚህ መብቶች ጋር ተያይዞ፣ የብሄረሰቦች የእኩልነት መብት በቃልና በፕሮግራሞች ብቻ ሳይሆን፣ በግብር መታወቅ አለበት፡፡ የያንዳንዱም ብሄረሰብ ቋንቋ፣ ባህል፣ ሃይማኖትና ሌሎችም መለያዎች በእኩልነት መታወቅና መከበር አለባቸው፡፡ እያንዳንዱ ብሄረሰብ የራሱን አስተዳደር በየደረጃው ለመምረጥ የሚችልበት መንገድ ኪሁኑ መቀየስ አለበት፡፡ በኤርትራ ክፍለ ሃገር በመካሄድ ላይ ያለውን ከንቱ የወንድማማች ደም መፋሰስን ለማቆም እንዲቻል፣ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ሰፊውን የኤርትራ ህዝብ ማመን፣ ለሁለቱ ዋና ተገንጣይ ድርጅቶች በይፋ የውይይት ጥሪን ማድረግ አለበት፡፡

ሶስተኛ፡፡ አብዮቱ የፈጠራቸው ህዝባዊ ድርጅቶች፣ ማለትም የቀበሌ፣ የወዛደር፣ የገበሬና ሌሎችም ማህበራት የበለጠ ስልጣን አግኝተው አድሃሪውን ቢሮክራሲ በቁጥጥራቸው ስር እንዲያውሉት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሰፊው ህዝብ በነፃ ድርጊቶች ለራሱ አመቺ የሆኑትን ያስተዳደርና የስራር ዘዴዎችን እንዲፈጥር መንገዱ መከፈትና እስከዚያውም ግን የታወቁ የሲቪል ሆኑ የሚሊተሪ ቢሮክራቶችን ከስልጣን ቦታቸው አስወግዶ በተራማጆችና ባገርወዳድ ግለሰቦች መተካት ያስፈልጋል፡፡

አራተኛ፡፡ በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ የደርግ አባሎች ባጠቃላይ ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም፣ ከደርግ አባሎች አብዛኙ ክፍል አሁንም ቢሆን ለአብዮቱና ለሰፊው ህዝብ የቆመ መሆኑ ቢታወቅም፣ ባሁኑ ወቅት በርከት ያሉ በክፍለሃገር የተሰማሩ የደርግ አባሎች ካድሃሪያን ጋር ይገግመው ይሰለፋሉ፡፡ በደርግና በህዝብ መካከል መራራቅን ይፈጥራሉ፡፡ የህዝቡን ንቃት፣ ድርጅት፣ ትጥቅና ነፃ አብዮታዊ ድርጊቶችን በማበረታታት ፈንታ ያፍናሉ፡፡ አንዳንዶቹም ጭፍን ፋሺስታዊ ጭፍጨፋን በማካሄድ ላይ እንዳሉ አገር ያወቀው ነገር ነው፡፡ ስለዚህም፣ በክፍለሃገር የተሰማሩትና በድርጊታቸው ካድሃሪያን ጋር መሰለፋቸውን ያረጋገጡ የደርግ አባሎች እንዲነሱ ማድረግ ያሻል፡፡

አምስተኛ፡፡ በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ ክፍለሃገር ለሰርጎገቦች መስፋፋትና ለገሪተኛ በቀላሉ መወረር ሀላፊው ቢሮክራሲው ነው፡፡ እንደዚሁም፣ ሰፊውን ህዝብ በማመንና ፖለቲካን በማስቀደም ፈንታ፣ በወታደራዊ አስተሳሰብ በመመራት መንግስት በመሳሪያ ብዛትና በወጭ ሃይሎች ላይ መተማመኑን ይዞአል፡፡ የሶማሊያ ወረራ በተስፋፋባቸው ክፍለሃገር ውስጥም አርሶአደሩን በጥርጣሬ አይን በመመልከትና በብሄር ትምክህተኞችም በማስጨፍጨፍ ለአብዮቱና ለሚወዳት አገሩ ሊቀሰቀስና ሊሰለፍ ይችል የነበረው ሰፊ ህዝብ ጠቅላላውን አብዮቱን ወለቦ እራሱ በጥርጣሬ አይን እንዲመለከተው ተደርጓል፡፡ ከዚህም የተነሳ፣ ወይ ከሰርጎገቦች ጋር የተሰለፈ፣ ያለዚያም ደግሞ ከዚያም ከዚህም ሳይሆኑ ቤትና ንብረታቸውን በትነው ጫካዎች ውስጥ የሰፈሩ በርካታ የአርሶአደር ቤተሰቦች እንዳሉ የታወቀ ነው፡፡ ስለሆነም፣ ከነዚህ ሁሉ በሽታዎች ተላቅቆና ሰፊውን ህዝብ አምኖና አስታጥቆ በየአካባቢው የሰረጉትን ወራሪዎች በራሱ ሃይል እንዲቋቋም ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

እነዚህ እርምጃዎች በፍጥነት ከተወሰዱ፣ የተራማጆችን ህብረት ለማጠንከርና ብሎም የኢትዮጵያን የወዛደር ፓርቲ፣ ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩንና ህዝባዊ አብዮታዊ ጦሩን ለመመስረት እጅግ አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ አብዮቱ ስር የሰደደባቸውን ያገሪትዋን ክፍሎች በመገንባት፣ የውስጥና የውጭ አድሃሪያንን ደምስሶ አብዮቱ ግቡን እንዲመታና ያገሪትዋም አንድነት እንዲጠበቅ ለማድረግ ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች አብዮትን ይፈልጋሉ፡፡ የአብዮታዊት እናት አገርን ክብርና አንድነት ይሻሉ፡፡ ለብሄራዊ ነፃነታቸውና ህዝቦቹዋን በእኩልነት ያቀፈች ኢትዮጵያ እስከመጨረሻው ይዋጋሉ፡፡ ሰፊው ህዝብ ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶ ሃይሉን ለዚህ የተቀደሰ ፍላጎቱ የሚያውልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ኢትዮጵያን ባፍሪካ ምድር እውነተኛ የአብዮት ምሽግ ለማድረግ እንችላለን፡፡

4. መኢሶን የሚያቀርባቸው ጥሪዎች

አንደኛ፡፡ ለጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፣ በተለይም በዚያ ውስጥ ላሉት ተራማጆች የምናቀርበው ጥሪ፣ በስሜትና በችኩልነት እንዳይመሩ ነው፡፡ ጥቂት የመኢሶን ጓዶች ትግላቸውን በጥብቅ ህቡእ እንዲቀጥሉ ድርጅቱ ስለወሰነ፣ መኢሶን ፣ቋሚ የመንግስት ስልጣን ለመያዝ ይፈልጋል በሚል ስህተተኛ አስተሳሰብ በመመራት፣ የመኢሶን አባሎች ወይንም ደጋፊዎቻቸው ተብለው በሚጠረጠሩ አብዮታውያንና አገርወዳዶች ላይ መንግስት ምንም አይነት የጭቆና እርምጃን መውሰድ የለበትም፡፡ መኢሶን ይህንን ውሳኔ ያደረገው ለአብዮቱ የወደፊት እርምጃ የበለጠ አስተዋጽኦን ለማበርከት እንዲያስችለው ብቻ እንጂ፣ ስልጣንን ባቋራጭ ለመያዝ አይደለም፡፡

..../5

መኢሶን ለሰፊው ህዝብ ስልጣን እንጂ፣ አንዳንድ አርናባጆች እንደሚሉት፣ ራሱን በስልጣን ላይ ለማስቀመጥ አይታገልም::ነገር ግን መንግስቱ ይህንን ሃቅ ስቶ በተራማጆችና በአገርወዳድ ግለሰቦች ላይ በግልጽም ይሁን በስውር የጭቆና እርምጃዎችን መውሰድ ከጀመረ፣ ያሉትን የአብዮቱንና ያገሪቱን ችግሮች ያባብሳቸዋል::በኢትዮጵያ ምድር ላይ የሱዳንና የቺሌ ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩም ያሰጋል::ስለዚህም፣ አብዮቱንና አገሪቱን ከውድቀት ለማዳን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ትእግስትንና አርቆአስተዋይነትን ይጠይቃል::የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ትልቅ ጥንቃቄን ማድረግ ይኖርበታል::

ሁለተኛ::ለኢትዮጵያ ሃቀኛ ተራማጆች የምንለው፣ መኢሶን አሁንም የሃቀኛ ተራማጆችን ህብረት እንደሚፈልግ ነው::እስካሁን የተፈጠረው ህብረት የይስሙላ እንጂ፣ እውነተኛ ህብረት አልነበረም::በህብረቱ ውስጥ እኩልነት የለም::ህብረቱ በዲሞክራሲና በቁምነገሮች የሚመራ አይደለም::በህብረቱ ውስጥ ቀጥ ያለው ያሰራር ዘዴ የለም::እንዲያውም አሁን የተያዘው ግልጽ አዝማሚያ ህብረቱን የቢሮክራሲው ተቀጥላ ድርጅት ለማድረግ ነው::

አንዳንድ የህብረቱ አባል ድርጅቶች አባሎች፣ ሃቀኛ የፖለቲካና የርእዮተአለም ትግልን በማካሄድ ፈንታ፣ በመኢሶን ላይ የጆሮጠቢና የሰብቀ ስራዎችን ሲያካሂዱ ቆይተዋል::ህዝቡን እንዴት እናንቃው፣ እንዴት እናደራጀው እያሉ በመጨነቅ ፈንታ፣ መኢሶን ምንድነው የሚሰራው፣ ማንን ነው የሚያደራጀው፣ ከማን ጋር ግንኙነት አለው?...ወዘተ. የሚሉትን የስለላ ጥያቄዎችን መከታተልና ከዚያም በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ማሳበቅን ስራቸው ብለው ከያዙት ውለው አድረዋል::

መኢሶን አሁንም ቢሆን የተራማጆችን ህብረት በጥብቅ ይፈልጋል::ነገር ግን ከብረት የጠነከረ ህብረት ሊፈጠር የሚችለው ከአድርባይነት፣ ለስልጣን፣ ለቦታና ለስም ከመስገብገብ፣ ይልቁንም ደግሞ ሰፊውን ህዝብ ከመፍራት ነፃ ሆነን፣ በሀቅና በዲሞክራሲያዊ ስነስርአት በሰፊው ህዝብ ፊት ስንናገር ነው::ያለበለዚያ በጥቂት ግለሰቦች መካከልና ከሰፊው ህዝብ በስተጀርባ፣ በሰፊው ህዝብ ሳይገለፁ፣ የሚካሄዱት የህብረት ውይይቶችና ስምምነቶች የቤተመንግስት ጨዋታዎች እንጂ አብዮታዊ ስራዎች አይሆኑም::እውነተኛ ህብረትን ለመፍጠር ከተፈለገ፣ በልዩነት ነጥቦች ላይ ሁሉ፣ የየድርጅቶቹ አባሎች በሙሉና ሰፊው ህዝብም ምንም አይነት ተጽእኖ የሌለባቸው ዲሞክራሲያዊ ክርክሮችን ለማካሄድ መቻል አለባቸው::

ሶስተኛ::የኢትዮጵያ ወዛደሮች፣ አርሶአደሮች፣ መለዮለባሾች፣ የጭቁን ብሄረሰቦች ታጋዮች፣ ጭቁን ሴቶች፣ ታጋይ ወጣቶች፣ ዲሞክራቲክና አገርወዳድ ግለሰቦች ሁሉ፣ ከላይ ለተጠቀሱት ለአብዮቱና ላገሪቱ ማዳኛ እርምጃዎች በቁርጠኝነት እንዲታገሉ መኢሶን ጥሪ ያደርግላቸዋል::

አብዮቱንና አገሪቱን ከውድቀት ሊያድን የሚችለው ሃይል የናንተ ትግል ብቻ ነው::ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ንቃታችንን፣ ድርጅታችንን፣ ትጥቃችንንና አንድነታችንን ማጠናከር አለብን::ባሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ጥቁር የፀረአብዮት ደመና ቢያንዣብብም፣በሶማሊያ ወረራ በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ አንዳንድ ቦታዎች ቢያዙም፣ አገራችንን ብሩህ የእኩልነት፣ የሰላም፣ የብልጽግናና የስልጣኔ ዘመናት ይጠብቋታል::የኢትዮጵያ ህዝቦች ለነፃነትና ለእኩልነት፣ ለሰላምና ለወደፊት እርምጃ የሚያደርጉት ትግል እንደዛሬ አመቺ ሁኔታን አግኝቶ አያውቅም::ችግሮቻችንንና ድክመቶቻችን፣ የአብዮታችን መቦርቦርና ያገራችን መወረር ጊዜያዊ ናቸው::ዘላቂነት የላቸውም::የፖለቲካ መስመር ትክክለኛነት ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ፣ ፖለቲካን አስቀድመን፣ ችግርንና ሞትን ሳንፈራ፣ በሰፊው ህዝብ ተማምነን እስከመጨረሻው ለመታገል ቆርጠን ከተነሳን፣ አንድነታችንን አጠንክረን ወደፊት ከተራመድን፣ የፈጀውን ጊዜ ቢፈጅና የፈለገውን መስዋእትነት ቢጠይቅም በርግጥ እናሸንፋለን::

ለአገሪቱ አንድነትና አብዮቱን ለማራመድ ህዝቡን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልጉ ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁኑኑ!

የብሄር ትምክህተኝነት ይውደም! የብሄረሰቦች ሙሉ እኩልነት ይኑር!

ፊውዶ—ቡርዧውን ቢሮክራሲ ለመደምሰስ እንታገል!

ሰፊው ህዝብ ይታጠቅ!

ሃቀኛ የተራማጆች ህብረትን እንመስርት!

የነፃ፣ የተደራጀና የታጠቀ የሰፊው ህዝብ አመጽ ያሸንፋል!